ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት. ዴ. ፓ)
Tigray Democratic Party (T.D.P)

የወቅቱ የሐገራችን ፈተናና መፍትሄው!

ከትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ት.ዴ.ፓ) የተሰጠ መግለጫ

ጥቅምት 2፣ 2013 ዓ/ም

የህወሓት/ኢህአዴግ አመራር መላው ኢትዮጵያን ለ27 ዓመታት በአምባገነንነት ገዝቶ፣ ብልሹ አስተዳደር አስፍኖ፣ ሙስናና ስርዓት አልበኝነትን ተቋማዊ አሰራር እስኪመስል ድረስ አስፋፍቶ፣ በመጨረሻም በህዝባዊ አመፅ ተገፍትሮ መቐለ ሄዶ እንዲመሸግ መገደዱ በግልፅ የሚታይ ክስተት ነው።

እዛው ሆኖም እራሱ በፈታውራሪነት ያስረቀቀው ሕገ-መንግስት አይገዛኝም በማለት የህዝብ ተወካዮች እና የፌደሬሽን ምክርቤቶች እንደዚሁም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የሚያስተላልፋቸውን ሕጋዊና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን በመጣስ ከተጠያቂነት የሚያመልጥበት የወንጀለና ሽፍታ ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

ይባስ ብሎም የመገንጠል ዓላማውን የሚያራምዱለት ቡድኖች ፈጥሮ የተገነጠለ መንግሥት (de facto state) ለመመስረትና ይህንኑ ግንጠላ ለማሣካት ወታደራዊ ኃይል ፈጥሮ ወደ ጦርነት ለመግባት ደፋ ቀና በማለት ይገኛል። የህዝቡ የኑሮ ሁኔታና የወጣቱ ስራ-አጥነት እንደ ድሮው ከምንም ሳይቆጥር ቡድናዊ ህልሙን ብቻ ለማስቀጠል እሱን የመሰሉ ስግብግብ ቡድኖች በመላ ኢትዮጵያ እያሰማራ ሀገሪቱን ለእርስ በርስ ግጭት እየዳረገ ለመሆኑ በበርካታ ክልሎች የሚታዩት ትንኮሣዎች ማስረጃዎች ናቸው።

የኤርትራ ግንጠላ እንዳይበቃን አሁንም ተጨማሪ ግንጠላዎች ለማሣካት ሀገራችን ጭራሽ እንድትበታተን ያቀደ እኩይ ተግባር እንደሆነ በአፅንኦት ሊታወቅ ያስፈልጋል። ይህ አካሄድ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ በኋላ በቻይናው እርስ በርስ ጦርነት ሣብያ በኩሚንታንግ የተመራው የታይዋንን ግንጠላ፣ በናይጀሪያ የባያፍራ የመገንጠል ሙከራና ያስከተለው እልቂት፣ እንደዚሁም በጎረቤት ሀገሮች የደቡብ ሱዳንና የሰሜን ሶማሊያ ግንጠላዎችን ተከትሎ የመጣ አደገኛና አፍራሽ ሂደት ነው።

ይህን ምንም ዓይነት እርባና የሌለው የህወሓት አመራር ፀረ-ህዝብ አካሄድ በመገንዘብ ብሎም የህዝቦች አንድነትና የሀገር ሉዓላዊነት በሚያጠናክር መልኩ በቅርቡ የፌደሬሽን ምክርቤት እርምጃዎች እንዲወሰዱ መወሰኑ ተገቢና ወቅታዊ ነው እንላለን። የህወሓት አመራር በለውጥ ማዕበል ተገፍቶ አምባገነናዊ ሥልጣኑንና ያግበሰበሰውን ሃብት ሲያጣ፣ የለውጥ ተቃዋሚና ለውጡንም ለመቀልበስ እንደሚጥር የሚጠበቅ ነበር። ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ የለውጥ አራማጁ ወገን፣ ፀረ-ለውጡ የቆመው የህወሓት ሃይልን ለመቆጣጠር ብሎም ሰይጣናዊ ህልሙን እንዳያሳካው ወቅታዊ እርምጃ በመውሰድ ላይ የዘገየ ቢሆንም አሁን የፌደሬሽን ምክርቤት ያስተላለፈው ውሳኔ ለትግራይ ህዝብና ለለውጥ ፈላጊው ወገን ሁሉ አበረታች መሆኑን እየገለፅን የትዴፓን አቋም ቀጥሎ እናቀርባለን፤

1. በትግራይ ክልል የሚገኘው ኢሕገ-መንግሥታዊ ክልላዊ አስተዳደር በሙሉ በህገ ወጡ የህወሓት አመራር ቁጥጥር ስር በመሆኑና ክልሉን ከአፋኝ አስተዳደር አላቆ በህዝባዊ አስተዳደር ለመተካት፣ እንዲሁም የፌደሬሽን ምክርቤት ያስተላለፈውን ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ ግድ ስለሚል ውሳኔውን የሚደግፉ፣ ፖለቲካዊና የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች (ትዴፓንና ፌደራል መንግሥትን ጨምሮ) ያቀፈ ጊዜያዊ የአስተዳደር ኮሚቴ በማቋቋም ውሳኔውን ማስፈፀም፣

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
ልደታ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 03፣ ፖፓሲኖስ ሕንፃ 3ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 909/33፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 59፣ መቐለ

2. በትግራይ ክልል ሁሉንም ተፎካካሪ ሀይሎች ያሳተፈ ዴሞክራሲያዊና ነፃ ምርጫ ለማካሄድ ሠላማዊ ምሕዳርን መፍጠር ቅድመ-ሁነት በመሆኑ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት (የኢትዮጵያ ፌደራል ሠራዊት) በዚህ ረገድ ህገ-መንግሥታዊ ግዴታውን እንዲወጣ እንጠይቃለን፤

3. በትግራይ ክልል ውስጥ ያለው «ልዩ ኃይል» አንድም በፌደራል ሠራዊት ማዕቀፍ ሥር፣ አልያም በፌደራል ፖሊስ እዝ ሥር ተጠቃሎ ህገ-መንግሥታዊ ግዳጁን እንዲፈፅም ማስቻል፣

4. ከትግራይ ክልል ውጭ በህገራቸው በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ ተጋሩ ኢትዮጵያዊያን በሸሸው የህወሓት አመራር ኃጥያት ሳቢያ የሚደርስባቸው ተፅዕኖ/ወከባ ካለ ለማስታገስና መብታቸውን በማስከበር ረገድ ሁሉም መንግሥታዊ አካላት ሆኑ ከቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተከታታይ መግለጫ የታጀበ የማረጋጋት ሥራ እንዲሠሩ፣

5. የህወሓት አመራር፣ እና ድርጅቱ ህወሓት የህጋዊው ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን የጣሰ በመሆኑና ግንጡል ምርጫም በማካሄዱ፣ ይህን ከህገመንግሥቱ ያፈነገጠ ድርጅትና አጃቢዎቹ «ፓርቲዎች» ከምርጫ ቦርድ የተሠጣቸውን እውቅና አሁንኑ እንዲሠረዝ አጥብቀን እንጠይቃለን፤

6. በፌደራል መንግሥት ይሁን በሌሎች መንግሥታዊ አካላት የሚወሰዱ እርምጃዎች ህገ-መንግሥቱን የተከተሉና ሠላማዊ እንዲሆኑ ስናሳስብ የትግራይ ህዝብ ጥቅሞችና ሠላማዊ ኑሮ በማይጎዳ መልኩ እንዲሆን በአፅንኦት እናሳስባለን፤

7. የህወሓት አመራር የጦርነት ቅስቀሳ ለግንጠላ መሣሪያነት እየተጠቀመበት መሆኑ ቢታወቅም የፌደራል መንግሥት ለሠላማዊ መፍትሄ ብቻ መትጋቱ የሚደነቅና ትዴፓም የሚያከብረው ተግባር ነው። ከቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለትግራይ ህዝብ «አንድ ጥይት ከመላክ ይልቅ አንድ ፀረ-ኮሮና ማስክ መላክ ይመረጣል!» እንዳሉት አሁንም አንድ የውጊያ ሄሊኮፕተር ከመላክ ይልቅ አንድ ፀረ-አንበጣ ሄሊኮፕተርን መላክ ይመረጣል ብለው እንዲተገብሩት እንጠይቃለን።

8. የፌደራል መንግስት ለህዝቡ ቀጥታ በሚሰጠው ግልጋሎት ህወሓት እንቅፋት ሊፈጥር እንድሚችል ግልጽ ነው። የትግራይ ህዝብ ይህንን ተገንዝቦ መብቱና ጥቅሙ እንዲጠበቅለት ህወሓትን በህግ እንዲገዛ እንዲያስገድደው ካልሆነም ከስልጣኑ ፈንቅሎ እንዲጥለው ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ት.ዴ.ፓ

ስልክ ቁጥር +251-118-65-13-36/+251-940-79-08-22/+251-914-73-35-39
Website: tigraydemocraticparty.com, email: tigraydemocraticparty@gmail.com
ልደታ ክፍለከተማ፣ ወረዳ 03፣ ፖፓሲኖስ ሕንፃ 3ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 909/33፣ አዲስ አበባ፣
ገብረየሱስ ሕንፃ 5ኛ ፎቅ፣ የቢ.ቁ. 59፣ መቐለ